# የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 559/2013

## 1. መግቢያ

1.1 የተሻሻለዉን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ቁጥር 558/2013ን (ከዚህ በኋላ "ደንብ" በመባል ይጠቀሳል) ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ (ከዚህ በኋላ "የምርት ገበያ" በመባል ይጠቀሳል) በምርት ገበያዉ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 550/1999 አንቀጽ 12(10) መሠረት ይህንን ደንብ ማሻሻያ አወጥቷል፡፡

1.2 ይህን የወስጥ ደንብ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ ይጠቀሳል) በባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 551/1999 አንቀጽ 6(3) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ካፀደቀዉ በኋላ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

1.3 ይህ የወስጥ ደንብ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የወስጥ ደንብ ማሻሻያ ቁጥር 559/2013" በመባል ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የተሻሻለዉ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ **የወስጥ** ደንብ ቁጥር **553/2013** (ከዚህ በኋላ "ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል) እንደሚከተለዉ እንደገና ተሻሽሏል፡፡

(1) የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 2.1.16 በደንቡ አንቀጽ 2.1 ስር ተጨምሯል፡፡ ከንዐስ አንቀፅ 2.1.16 እስከ 2.1.47 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 2.1.17 እስከ 2.1.48 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"**2.1.16** በንግድ ላይ የተሰማራ የግብርና አምራች – አልሚ ባለሃብት እና የእርሻ ድርጅትን ጨምሮ፣ የግብርና ምርትን ለገበያ ለማቅረብ የሚያመርት ማንኛዉም ሰው ነው፡፡"

(2) የሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀጾች 2.1.49 እና 2.1.50 በደንቡ አንቀጽ 2.1 ስር ተጨምረዋል፡፡ ከንዐስ አንቀፅ 2.1.49 እስከ 2.1.65 የነበሩት ከንዐስ አንቀፅ 2.1.51 እስከ 2.1.68 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"2.1.49 አቀናባሪ – የግብርና ምርት ላይ የማቀናበሪያ ኢንዱስትሪ ተጠቅሞ በሚፈተግ፣ በመቁላት ወይም በይዘት እና ማጠን ላይ እሴት በሚጨምር ለገበያ ዝግጁ አድርጎ የሚያቀርብ ማንኛዉም ሰው ነው፡፡"

2.1.50 "ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከል – በምርት ገበያው ከአዲስ አበባ ውጭ የሚከፈት የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከል ነው፡፡"

(3) የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.1.1 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.17.1.1 የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚከተሉት **አምስት** ዓይነት አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ይኖሩታል።

ሀ. አነስተኛ የግብርና አምራቾች

ለ. አቅራቢዎች

ሐ. ላኪዎች

መ. አቀናባሪዎች እና

ሠ. በንግድ ላይ የተሰማሩ የግብርና አምራቾች"

**(4)** የደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17.3.2 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡፡

"4.17.3.2.1 አቅራቢ፣ ላኪ፣ አቀናባሪ ወይም በንግድ ላይ የተሰማሩ የግብርና አምራች ከሆነ ግዙፍነት የሌለዉ ወይም በእጅ የሚዳሰሰትን ንብረት በመቀነስ የሚገኘውን የተጣራ ንብረት ሊያሟላ የሚገባውን አነስተኛውን መጠን ስለማሟላቱ የሚያረጋግጥ በባለሥልጣኑ ዕውቅና ባገኘ ኦዲተር የተመረመረ የፋይናንስ መግለጫ ብር 250,000 ካቀረበ፤

4.17.3.2.2 በንኡስ አንቀጽ 4.17.3.2.1 የተገለጸው ቢኖርም በክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚከሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አቅራቢ የሆነ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ የተጣራ ንብረት ስለማሟላቱ የሚያረጋግጥ የፋይናንስ መግለጫ ሚረጋገጫ ማምጣት ሳይጠበቅበት ማበያየት ይችላል፡፡

4.17.3.2.3 አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ሆኖ ለማበያየት የሚጠየቀውን የመግቢያ ክፍያ ከከፈለ፡-

ሀ. ለአቅራቢ፣ ላኪ፣ አቀናባሪ ወይም በንግድ ላይ የተሰማሩ የግብርና አምራች ብር 25,000፤

ለ. በንኡስ አንቀጽ 4.17.3.2.3 (ሀ) ላይ የተገለጸው ቢኖርም በክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚከሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አቅራቢ ወይም በንግድ ላይ የተሰማሩ የግብርና አምራች ብር 5,000፣

4.17.3.2.4 አቅራቢ፣ ላኪ፣ አቀናባሪ ወይም በንግድ ላይ የተሰማሩ የግብርና አምራች ወይም ላኪ ከሆነ ለምርት ገበያው የግዴታ ሚዲጸሚያ ዋስትና ማቋቋሚያ የሚሆን ብር 50,000 ከወለድ ነፃ የሆነ የዋስትና ተቀማጭ በጥሬ ገንዘብ ከከፈለ፤

4.17.3.2.5 በንኡስ አንቀጽ 4.17.3.2.4 የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም በምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚከሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አቅራቢ የሆነ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ለምርት ገበያው የግዴታ ሚዲጸሚያ ዋስትና ማቋቋሚያ የሚሆን የዋስትና ተቀማጭ ብር መክፈል ሳይጠበቅበት ግብይት ማከናወን ይችላል፡፡

4.17.3.2.6 አቅራቢ፣ ላኪ፣ አቀናባሪ፣ ወይም በንግድ ላይ የተሰማራ የግብርና አምራች ከሆነ አሥቃዊ የእድሳት ክፍያ ብር 5,000 ከከፈለ

4.17.3.2.7 በንኡስ አንቀጽ 4.17.3.2.6 የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም በምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አቅራቢ ወይም በንግድ ላይ የተሰማራ የግብርና አምራች ከሆነ አሥቃዊ የእድሳት ክፍያ ብር 3,000 ከከፈለ፤"

**(5)** የሚከተለዉ አዲስ ንኡስ አንቀጽ 4.17.8 በደንቡ ንኡስ አንቀጽ 4.17 ስር ተጨምሯል፡፡ ከደንቡ ንዑስ አንቀፅ 4.17.8 እስከ 4.17.13 ያሉት ከንዐስ አንቀፅ 4.17.9 እስከ 4.17.14 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

"**4.17.8** በክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ስለማበያየት

4.17.8.1 በምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ በሁሉም የምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት ማበያየት ይችላል፡፡

4.17.8.2 ማንኛውም በምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ይህንኑ አክብሮ ለማንቀሳቀስ የተስማማ መሆኑን በምርት ገበያው በተዘጋጀ ቅጽ በመሙላት በፊርማው በሚረጋገጥ ግዴታ መግባት ይኖርበታል፡

4.17.8.3 ማንኛውም በምርት ገበያው ክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠ አባል ያልሆነ ቀጥታ ተገበያይ ከክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት ውጭ በሚካሄዱ ግብይቶች ላይ ለመሳተፍ የሚችለው በንኡስ አንቀጽ 4.17.8.2 ላይ ተገለጸውን በምርት ገበያው የክልል የማበያያ ማእከል በሚካሄዱ ግብይቶች ብቻ ለማበያየት የሚጠበትን የግዴታ መግቢያ ሰነድ በማቋረጥ ከክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት ውጭ በሚካሄዱ ግብይቶች ላይ ለመሳተፍ የሚያስችለውን የመግቢያ መስፈርቶች እና ቅድመ ሁኔታዎች ያሟላ እና የምርት ገበያውን ፍቃድ ያገኘ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

4.17.8.4 ተገበያዮች ከክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት ወደ አዲስ አበባ የግብይት ማእከል ወይም ከአዲስ አበባ የግብይት ማእከል ወደ ከክልላዊ የኤሌክትሮኒክ የግብይት ማእከላት ለማበያየት ዝውውር ሲያካሂዱ ምርት ገበያው የተዛወሩትን ተገበያዮች ለባለስልጣኑ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡"

3. **ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን**

በደንቡ ንዐስ አንቀጽ 21 (1) መሰረት ይህ ደንብ በባለሥልጣኑ ከጸደቀ ከአስራ አራተኛው ቀን በ|ላ ተፈጻሚ ት ይኖረዋል።

በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ቦርድ ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ጸደቀ፡፡